-

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር...
አርባምንጭ ታህሳስ...ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No
Arbaminch December, 2023

አዋጅ ቁጥር ...../፪ሺ፲፮ ዓ.ም

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የየጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ

መግቢያ

የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት በተሻለ ሁኔታ ማስከበር፣ ጥራቱን የጠበቀና የተደራጀ የጥብቅና አገልግሎት አቅርቦት መኖር፣ እና የጥብቅና አገልግሎት የሥነ-ምግባር ደረጃን ማሳደግ ለሕግ የበላይነት፣ ለፍትሕ ተደራሽነት፣ ለማህበራዊ ፍትህ መስፈንና ለፍትህ ሥርዓት ተልዕኮ መሳካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሕዝብ ጥቅምን በማስጠበቅና ፍትሕን በማስፈን ዙሪያ የተደራጀ፤ የመንግስትና የሙያተኞችን ተዋጽዖ ያማከለ የጋራ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቀጣይነትና ድርጅታዊ ዋስትና ያለው የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የጥብቅና ድርጅት የሚመራበትንና የሚተዳደርበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ጠበቆች በተከታታይ ሥልጠና አማካኝነት በየጊዜው ከሚወጡ አዳዲስ ሕጎችና የሕግ ጽንሰ-ሀሳቦች ጋር የሚተዋወቁበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ጠበቆች በግላቸውም ሆነ በተደራጀ መልኩ መብት እና ጥቅሞቻቸውን የሚያስከብሩበትን፤ እንዲሁም እውቀት፣ ክህሎት እና ሥነ-ምግባራቸውን የሚያዳብሩበት ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር የሚነሱ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ፍትሐዊ ሥርዓት መደንገግ በማስፈለጉ፤

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ___/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡-

1. "ጠበቃ" ማለት የግል የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት በዚህ አዋጅ መሰረት የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤
2. "የጸና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፍቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን መስፈርቶች ላሟላ ሰው የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤
3. "የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመና የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፤
4. "የጥብቅና ሙያ አገልግሎት" ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚሰጥ ማንኛውም የሕግ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-
   ሀ) በሕግ ጉዳዮች ላይ ምክር መስጠት፣
   ለ) ከወንጀል ጉዳዮች ውጪ የማደራደር ሥራ፣
   ሐ) የሕግ ሠነድ ማዘጋጀት ወይም በደንበኛው ሥም ሰነድን ማቅረብ፣
   መ) በፍርድ ቤቶች፣ አስተዳደራዊ ጉባዔዎች፣ ከፊል የዳኝነት ሥልጣን ባላቸው አካላት እና በሌሎች አማራጭ የሙግት መፍቻ መድረኮች ደንበኛን ወክሎ መቅረብ እና መከራከር።
5. "የሕግ ሙያ አገልግሎት" ማለት በዳኝነት፣ በዓቃቤ ህግነት፣ በተከላካይ ጠበቃነት፣ በህግ መምህርነት፣ በረዳት ዳኝነት፣ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት ውስጥ በህግ ጉዳይ ጸሀፊነት ወይም በጠበቃ ረዳትነት፤ በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ወይም የንግድ ድርጅቶች ወይም በህዝማኖት ተቋማት ወይም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎች ተቋማት ውስጥ በህግ አማካሪነት ወይም በነገረ ፈጅነት ወይም በህግ ባለሙያነት ማገልገል ነው።
6. "የሕግ ጉዳይ ፀሐፊ" ማለት በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ሥር በመሆን በጠበቃ በኩል የሚቀርቡ ክሶችን፣ ማመልከቻዎችን፣ ይግባኞችን፣ አቤቱታዎችን፣ መልሶችን እና ሌሎች ሕግ ነክ ሠነዶችን በማዘጋጀት ወይም በመተየብ ጠበቃን የሚያግዝ ሰው ነው፤
7. "የጠበቃ ረዳት" ማለት በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ሥር በመሆን ለጠበቃው የሕግ አስተያየት የሚያዘጋጅ፣ የተዘጋጁ ክሶችን፣ ማመልከቻዎችን፣ ይግባኞችን፣ አቤቱታዎችን ወይም መልሶችን ፍርድ ቤት ወይም በሌላ የሕግ ሰውነት ባለው ተቋም ዘንድ በመገኘት የሚያቀርብ፤ ለሚመለከተው አካል የሚያደርስ፣ የክስ ወይም የይግባኝ መዝገብ የሚያስከፍት፤ መጥሪያዎችን፣ የውሳኔ ግልባጮችን እና ሌሎች ለጠበቃው መድረስ ያለባቸውን ሠነዶች ከሚመለከተው አካል በመቀበል ለጠበቃው የሚያደርስ ሰው ነው፤

8. “መዝገብ” ማለት በፍትህ ቢሮ የሚዘጋጅና የጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሙሉ መረጃ የሚመዘገብበት ባህር መዝገብ ወይም የመረጃ ቋት ነው፤

9. “የሥነ-ምግባር ደንብ” ማለት የጠበቆች እና ጥብቅና ድርጅቶች ሥነ-ምግባርን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ደንብ ነው፤

10. “ደንበኛ” ማለት የጥብቅና አገልግሎት ተቀባይ ሰው ነው፤

11. “አገናኝ” ማለት የጥብቅና አገልግሎትን በሚመለከት ጠበቃን ወይም የጥብቅና ድርጅትን እና ባለጉዳይን በማገናኘት ከአንዱ ወይም ከሁለቱም ወገን ክፍያ ወይም ኮሚሽን በመቀበል ወይም ወደፊት ለመቀበል በማሰብ ባለጉዳዩን በማግባባትና በማሳመን ባለጉዳዩ እርሱ የመረጠለትን ጠበቃ እንዲይዝ ለማድረግ ወይም ለማግባባት ጥረት የሚያደርግ ማንኛውም ሰው ነው፤

12. “የጥብቅና ሥራን በአገናኝ አማካኝነት መስራት” ማለት በፍርድ ቤቶች፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሌሎች የፍትሕ ተቋማት ወይም በማንኛውም ስፍራ አገናኞችን በማሰማራት ወይም በተሰማሩ አገናኞች ወይም ከየፍትሕ ተቋማቱ ኃላፊዎች ወይም ሠራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር የጥብቅና አገልግሎት ፈላጊዎች ወደ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ እንዲመጡ የማድረግ ተግባር ነው፤

13. “የታክስ ክሊራንስ” ማለት አንድ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሰው ላገኘው ገቢ ግብር ስለመክፈሉ ከግብር አስገቢው አካል የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

14. “ማኅበር” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 75 መሠረት የተቋቋመ የክልሉ ጠበቆች ማኅበር ነው፤

15. “ቢሮ” ወይም “የቢሮ ኃላፊ” ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የፍትህ ቢሮ ወይም የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ነው፤

16. “ሥልጠና” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በማኅበሩ ወይም ማኅበሩ እውቅና በሰጠው ተቋም አማካኝነት ለጠበቆች በሥራ ላይ እያሉ የሚሰጥ የሕግ ሥልጠና ነው፤

17. “ተቋም” ማለት ተከታታይ የሕግ ሥልጠና የሚሰጥ ድርጅት ነው፤

18. “ጉባኤ” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቋቋመ የጠበቆች አስተዳደር ጉባኤ ነው፤

19. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. <u>የዕታ አገላለጽ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ዕታ የተደነገገው የሴትንም ዕታ ያካትታል።

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ፍትሕ ቢሮ የጥብቅና ፈቃድ በተሰጠው ጠበቃ እና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>ስለጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ</u>

5. <u>የጥብቅና ፈቃድ መርሆዎች</u>

1. ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አይችልም፤

2. የጥብቅና ፈቃድ ቋሚ ሥራ ላለው ሰው አይሰጥም፤

3. ማንኛውም የጥብቅና ፈቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰው በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፤

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰው በጾታ፤ በሃይማኖት፤ በቋንቋ፤ በዘር ወይም በማኅበራዊ አመጣጡ፤ በፖለቲካ አመለካከቱ፤ በንብረቱ፤ በትውልዱ፤ በአካል ጉዳት ወይም ማንኛውንም ተመሳሳይ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ፍቃድ አይከለከልም።

6. ፈቃድ የማያስፈልግበት ሁኔታ

የሚከተሉት አካላት የጥበቅና ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው የጥበቅና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡-

1. ስለራሱ ጉዳይ የሚከራከር ሰው፣
2. ያለክፍያ ለትዳር ጓደኛው፣ ለወላጁ፣ ለልጁ፣ ለአያቱ፣ ለእህቱ፣ ለወንድሙ፣ ለትዳር ጓደኛው ወላጆች፣ እንዲሁም ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰው የሚከራከር ሰው፣
3. ከሥራው ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚከራከር ዐቃቤ ሕግ፣
4. ሕጋዊ ሰውነት ባለው የንግድ ድርጅት፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት፤ ሕዝባዊ ድርጅት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የሙያ ማኅበር ወይም በሌላ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት በተቋቋመ ድርጅት ተቀጥሮ የተወከለ ሰው፣
5. የመንግስት መሥሪያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚመለከት የሚከራከር ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰው፣ ወይም
6. ማንኛውም የሠራተኛ ማኅበር መሪ ወይም ማህበሩ የሚወክለው ሰው።

7. ፈቃድ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

1. ማንኛውም በጥበቅና ሙያ መሰማራት የሚፈልግ ሰው የጥበቅና ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ) በህግ ትምህርት እውቅና ካለው የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ ዲፕሎማ ያለው፣

ሐ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ እና የመልካም ሥነ-ምግባር ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

መ) በሕግ ሙያ የሚፈለገውን የሥራ ልምድ የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሠ) እንደ አስፈላጊነቱ ፈቃድ ለማግኘት የሚሰጠውን የሙያ መግቢያ ፈተና ማለፉን የሚያሳይ ማስረጃ፣

ረ) ቋሚ ሥራ ከነበረው ከሚሰራበት መስሪያ ቤት የተሰጠውን የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ፣ እና

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ሀ እስከ ረ የተዘረዘሩ ሰነዶችን በማያያዝ የጥበቅና ፈቃድ ማመልከቻውን ለቢሮው ማቅረብ ይኖርበታል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት የሚቀርበው የፈተና ውጤት ዋጋ የሚኖረው ውጤቱ በታወቀ 3 ወራት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ብቻ ነው።

8. ፈቃድ የማያሰጡ ምክንያቶች

ማንኛውም ሰው የጥበቅና ፈቃድ የማይሰጠው፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ፣
2. ታስቦ በሚፈጸምና ከሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ እና አግባብነት ባለው ሕግ ያልተሰየመ ከሆነ፣

3. በሕግ አገልግሎት እንዳይሰማራ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ ከሆነ ነው።

9. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የክልሉ የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ የሚሰጠው በቢሮው ነው፤
2. አመልካቹ በዚህ አዋጅ መሰረት የተሟላ ማመልከቻ ባቀረበ በ 3 የስራ ቀናት ውስጥ ቢሮው ተገቢውን ውሳኔ መስጠት አለበት፤
3. የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ ቢሮው ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት በ 5 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፤
4. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 መሰረት ፈቃድ እንዲሰጥ በወሰነ በ 3 የስራ ቀናት ውስጥ የጥብቅና ፈቃዱን ለአመልካቹ መስጠት አለበት፤
5. የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ በፈቃድ ደብተር ላይ መጠቀስ ያለባቸው ነጥቦች ዝርዝር ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
6. ቢሮው ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገው አመልካቹ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በ 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለጉባኤው ማቅረብ ይችላል፤
7. በጉባኤው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የውሳኔ ግልባጭ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

10. <u>የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች</u>

1. የክልሉ የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣
2. የክልሉ የማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣ እና
3. የክልሉ ልዩ ጥብቅና ፈቃድ ናቸው።

11. <u>የክልሉ የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ</u>

የሚከተሉትን መስፈርቶች ላሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የክልሉ የወረዳ ወይም የከተማ መጀመሪያ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፡-

1. በህግ ትምህርት እውቅና ካለው የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው እና በሕግ ሙያ ቢያንስ ሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ወይም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀ እና በሕግ ሙያ አራት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣
2. ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ያለፈ፣
3. ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ፣ እና
4. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል።

12. <u>የክልሉ ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ</u>

የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የክልሉ ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፡-

1. በህግ ትምህርት እውቅና ካለው የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው እና በሕግ ሙያ ቢያንስ አራት ዓመት የሥራ ልምድ ወይም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀ እና በሕግ ሙያ ስድስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣
2. እንደ አስፈላጊነቱ ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና ፈቃድ መግቢያ ፈተና ያለፈ፣
3. ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ፣ እና

4. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል።

13. <u>የክልሉ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ</u>

1. በክልሉ የሕብረተሰቡን አጠቃላይ መብትና ጥቅም ለማስከበር በነጻ የህግ አገልግሎት ለሚሰጥ የሚከተሉትን መስፈርቶች ለሚያሟላ ሰው ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጠዋል፦

ሀ) በህግ ትምህርት እውቅና ካለው የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው እና በህግ ሙያ ቢያንስ 4 ዓመት ያገለገለ ወይም በሕግ በዲፕሎማ የተመረቀ እና በህግ ሙያ ቢያንስ 6 ዓመት ያገለገለ፣

ለ) ከሚወክለው የሕብረተሰብ ክፍል ወይም ደንበኛ ክፍያ የማይቀበል፣ እና

ሐ) መልካም ሥነ-ምግባር ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ማቅረብ የሚችል።

2. ማንኛውም የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ ያለው ሰው ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ሳያስፈልገው የልዩ ጥብቅና አገልግሎት መስጠት ይችላል፤ ነገር ግን ይህን አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ለቢሮው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አቅም ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነጻ የህግ ድጋፍ ለሚሰጡ የሕግ ፋክሊቲ ላላቸው ዩኒቨርሲቲዎች ወይም ለዚሁ ዓላማ ብቻ ለሚቋቋሙ ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤

4. የክልሉ ልዩ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት የጥብቅና አገልግሎቱን ሲሰጥ ይህን አዋጅ እና የጠበቃ ሥነ-ምግባር ደንብን በተከተለ መልኩ መፈጸም አለበት።

14. <u>ለሕግ መምህራን ስለሚሰጥ የጥብቅና ፈቃድ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገገው ቢኖርም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምር የሕግ መምህር በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰውን ካሟላ የሕግ መምህርነት ሙያውን መልቀቅ ሳያስፈልገው የጥብቅና ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሕግ ትምህርት ቤት መምህር የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት የጥብቅና ሥራው የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያስተጓጉል ስለመሆኑ በሕግ ትምህርት ቤቱ የተሰጠ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት።

15. <u>ስለ ጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገጉትን የሚያሟላ ማንኛውም በጥብቅና አገልግሎት መሰማራት የሚፈልግ ሰው የመመዝገቢያ ክፍያ በመፈጸም የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና መውሰድ ይኖርበታል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የሚከተለው የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ያላቸው የህግ ባለሙያዎች የጥብቅና ፈቃድ ያለፈተና ሊሰጣቸው ይችላል፦

ሀ) በህግ ትምህርት ዕውቅና ካለው የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ያለውና በዳኝነት፣ በዐቃቤ ሕግነት፣ በተከላካይ ጠበቃነት፣ በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ውስጥ በሕግ አማካሪነት ወይም በሕግ ባለሙያነት ወይም በነገረ ፈጅነት ቢያንስ የአራት ዓመት አገልግሎት ያለው፣ ወይም

ለ) በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በሕግ መምህርነት ቢያንስ ለ 5 ዓመት ያገለገለ፣

ሐ) በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በረዳት ዳኝነት፣ በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት የሕግ ጉዳይ ጸሐፊነት ወይም የጠበቃ ረዳትነት እንዲሁም በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በንግድ ድርጅቶችና ሌሎች ተቋማት በሕግ አማካሪነት ወይም በሕግ ባለሙያነት ወይም በነገረ-ፈጅነት ቢያንስ የስድስት ዓመት አገልግሎት ያለው፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም ቢሮው ያለፈተና ፈቃድ የሚሰጠው አመልካቹ ሥራውን በለቀቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፈቃድ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ ነው።

16. <u>የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ ስለማሻሻል</u>

1. በክልሉ የወረዳ ወይም ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ጥብቅና ፈቃድ ያለው ጠበቃ የስራ ልምዱ እና የትምህርት ደረጃው የክልሉን ማናቸውም ፍርድ ቤቶች የጥብቅና ፈቃድ የሚያሰጠው ከሆነ ደረጃው እንዲሻሻልለት ለቢሮው ማመልከት ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም በክልሉ የወረዳ ወይም ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥብቅና ፈቃድ ያለው ጠበቃ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በጥብቅና ፈቃዱ ለአራት ዓመት እንዲሁም በህግ ዲፕሎማ ኖሮት በጥብቅና ፈቃዱ ለስድስት ዓመት ካገለገለ የጥብቅና አገልግሎት ሥራውን ሳይተው የክልሉ ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ ያለፈተና ሊሰጠው ይችላል።

17. <u>ቃለ መሐላ ስለማስፈጸም</u>

ማንኛውም የጥብቅና አገልግሎት ፈቃድ የሚሰጠው ጠበቃ የሚከተለውን ቃለ መሀላ በጽሑፍ ማረጋገጥ አለበት፦-

«እኔ-------- ዛሬ------ ቀን-------- ዓ.ም የክልሉን የጥብቅና ፈቃድ ስቀበል የሀገሪቱንና የክልሉን ሕገጋት-መንግስታት እና ሕጎች ላከብር እና ላስከብር፤ ለፍትሕ ሥርዓቱ ተልዕኮ መሳካት በመልካም ሥነ-ምግባር በሙያዬ በቅንነት እና በታማኝነት በመስራት የምወክላቸውን ደንበኞቼን ጥቅም ሕግ በሚፈቅደው አግባብ ላስከብር፤ ከተከራካሪዎቼ እና ከሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመግባባት እና በመከባበር ልሰራ እና ባለኝ እውቀት እና ችሎታ ለሕግ የበላይነት ተገቢውን እገዛ ለማድረግ ቃል እገባለሁ»

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ስለ ጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት</u>

18. <u>የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት ስለማቋቋም</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የጸና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ጠበቆች አንድ ላይ በመሆን የጥብቅና ድርጅት ማቋቋም ይችላሉ።

19. <u>የአገልግሎት ወሰን</u>

1. የጥብቅና ድርጅት ዋነኛ ተግባር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ነው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከጥብቅና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች አገልግሎቶች ሊሰጥ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

20. <u>የጥብቅና ድርጅት አደረጃጀት እና ኃላፊነት</u>

1. የጥብቅና ድርጅት ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር አደረጃጀት ይኖረዋል፤
2. የጥብቅና ድርጅት፦
   ሀ) ውል መዋዋል፣
   ለ) የንብረት ባለቤት መሆን፣
   ሐ) በሥሙ መክሰስና መከሰስ እና የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት የሚኖረው ሌሎች መብት እና ግዴታዎች ይኖረዋል፤
3. የጥብቅና ድርጅት ሽረኮች ለሶስተኛ ወገን የሚኖርባቸው ኃላፊነት በጥብቅና ድርጅቱ ውስጥ ባላቸው የመዋጮ ድርሻ ልክ የተወሰነ ይሆናል፤

4. የጥብቅና ድርጅት አባላትን የሚመለከት ለውጥ ቢመጣም የጥብቅና ድርጅት ህልውና ይቀጥላል፤

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት መስጠቱ በሀገሪቱ ወይም በክልሉ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ሕጎች መሠረት አገልግሎቱን የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ሥራ አያሰኘውም።

21. <u>ስለ ጥብቅና ድርጅት ሥያሜ</u>

1. የጥብቅና ድርጅት አባላት ማንኛውንም ሥያሜ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱ መጠሪያ እንዲሆን መምረጥ እና መወሰን ይችላሉ፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለጥብቅና ድርጅቱ መጠሪያነት የተመረጠው ሥም ቢሮው በሚከተሉት ምክንያቶች ተቀባይነት ላይኖረው የሚችለው፡-

   ሀ) ከሌላ የጸና የጥብቅና ድርጅት ሥም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣

   ለ) ደንበኞች ድርጅቱን ከሌላ የጥብቅና ድርጅት በቀላሉ መለየት እንዳይችሉ በሚያስችል መልኩ ሊያሳስት ወይም ሊያደናግር የሚችል ከሆነ፣ እና

   ሐ) ለሕግ ወይም ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆነ።

3. የጥብቅና ድርጅት ሥም የጥብቅና ድርጅት መሆኑን የሚያመለክትና ከሥሙ በስተመጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር" ወይም ("ኃ.የተ.የሽ.ማ") የሚል ሐረግ ያለው መሆን አለበት፤

4. በጥብቅና ድርጅቱ ሥም የሚወጡ ሠነዶች በሙሉ በግልጽ ሥሙን እና "ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር" የሚለውን ሐረግ መያዝ አለባቸው።

22. <u>የመቋቋሚያ መሥፈርቶችና ሥነ-ሥርዓቶች</u>

1. የጥብቅና ድርጅት በቢሮው በመመዝገብ ይቋቋማል፤

2. የጥብቅና ድርጅት ለማቋቋም የሚከተሉት ሠነዶች ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው ለቢሮው መቅረብ አለባቸው፡-

   ሀ) የሽሪኮቹን ሙሉ ሥምና ፊርማ የያዘ ማመልከቻ፣

   ለ) የድርጅቱን መመስረቻ ጽሑፍ፣

   ሐ) የሽሪኮቹ የጥብቅና ፈቃድ ቅጂ፣ እና

   መ) ሽሪኮች ድርጅቱን ለመመስረት የተስማሙበትን የሽርክና ስምምነት፣ የጥብቅና ድርጅቱን ሥም፤ የሽርክና ማኅበሩን የቆይታ ዘመን፤ የድርጅቱን ዓላማ በአጭሩ የተገለጸበት እና በምስረታ ሂደት ድርጅቱን የሚወክለው ሽሪክ የተሰየመበት ቃለ-ጉባዔ።

3. የጥብቅና ድርጅት መመስረቻ ጽሑፍ በንግድ ሕጉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር መመስረቻ ጽሑፍ ሊያካትታቸው የሚገቡ ዝርዝሮችን ማካተት ይኖርበታል፤

4. ቢሮው የቀረቡለት ሠነዶች ከዚህ አዋጅና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ካረጋገጠ ማመልከቻውን በተቀበለ በ 5 የሥራ ቀናት ውስጥ የጥብቅና ድርጅቱን ይመዘግባል፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

5. ቢሮው የቀረቡለት ሠነዶች ከዚህ አዋጅና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጎች ጋር የሚጣረሱ ናቸው ብሎ ካመነ ማመልከቻውን በተቀበለ በ 10 የሥራ ቀናት ውስጥ ውድቅ ማድረግና ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን መነሻ የሆነውን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ያቀረበው ማመልከቻ ውድቅ የተደረገበት አካል ቅሬታውን ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ባወቀ በ 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለጉባኤው ማቅረብ ይችላል፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ጉባኤው በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔ በተሰጠ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

23. <u>የመዋጮ ዓይነትና መጠን</u>

1. የጥብቅና ድርጅት ሸሪኮች ዋነኛው መዋጮ ክህሎት መሆን አለበት፤
2. ሸሪኮች መዋጮዎችን በገንዘብ ወይም በዓይነት ማዋጣት ይችላሉ፤
3. የጥብቅና ድርጅት ሸሪኮች የመዋጮ መጠን የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት የሚበቃ መሆን ያለበት ሆኖ በገንዘብ የሚደረገው መዋጮ ከሃምሳ ሺህ ብር ማነስ የለበትም፤
4. ገንዘብ ባልሆነ ማናቸውም መንገድ በጥብቅና ድርጅት ሸሪክ የሚደረግ መዋጮ ዋጋ በሁሉም ሸሪኮች ስምምነት እና አግባብነት ባላቸው ሕግጋትና ደንቦች ይወሰናል።

24. <u>የሸሪኮች መብትና ግዴታ</u>

1. የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

ሀ) በጥብቅና ድርጅቱ ስብሰባዎች የመካፈል እና ድምጽ የመስጠት፣

ለ) በድርሻው መጠን ከጥብቅና ድርጅቱ ትርፍ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስም ከተጣራው የማኅበሩ ሀብት ከሚተርፈው ሀብት የመካፈል፣

ሐ) የጥብቅና ድርጅቱን አጠቃላይ አሠራር የመከታተል፣ የማወቅ፣

መ) በሽርክና ስምምነት፣ በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከቱ ወይም ከሽርክና ማኅበሩ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች መብቶችና ጥቅሞችን የመጠቀም።

2. የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

ሀ) ለጥብቅና ድርጅቱ መክፈል የሚጠበቅበትን መዋጮ በወቅቱ መክፈል፣

ለ) በማናቸውም ጊዜ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት በትጋት የመሥራት፣

ሐ) ለራሱ ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆንም ባይሆንም የጥብቅና ድርጅቱን ጥቅም ከሚጻረሩ ድርጊቶች ወይም ኃላፊነትን ከሚያጓድሉ ተግባራት መታቀብ፣ እና

መ) በሽርክና ስምምነት፤ በዚህ አዋጅ፣ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች፣ በሽርክና ስምምነት የተመለከቱ ወይም ከሽርክና ማኅበሩ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች ግዴታዎችን የመወጣት።

25. <u>ትርፍ እና ኪሣራ ክፍፍል</u>

በጥብቅና ድርጅቱ የሽርክና ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የማኅበሩ ሸሪኮች የድርጅቱን ትርፍ እና ኪሳራ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስም ከተጣራው የማኅበሩ ሀብት የሚተርፈውን ሀብት በድርጅቱ ውስጥ ባላቸው ድርሻ መጠን የመካፈል መብት አላቸው።

26. <u>የሸሪኮች ለውጥ</u>

1. አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተጣለው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅቱን ለሚለቅ ሸሪክ የድርሻው ዋጋ እና የትርፍ ድርሻው ሊከፈለው ይገባል፤
2. የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ በሚሞት ጊዜ ሸሪኩ ሊከፈለው የሚገባ ያልተከፈለው የትርፍ ድርሻ ለሕጋዊ ወራሾቹ ይተላለፋሉ።

27. <u>ባለቤትነት</u>

የጥብቅና ድርጅት ባለቤት መሆን የሚችሉት የጸና የጥብቅና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆች ብቻ ናቸው።

28. <u>በጥብቅና ድርጅት ሥር በሚሠሩ ጠበቆች ላይ የተጣለ ክልከላ</u>

1. በጥብቅና ድርጅት ውስጥ ሸሪክ ሆኖ የሚሠራ ማንኛውም ጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ የሸርክና ወይም የሥራ ቅጥር ዘመኑ ጸንቶ ባለበት ጊዜ መሳተፍ የማይችልባቸው ተግባራት፡-

ሀ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሌላ የጥብቅና ድርጀት ሸሪክ ወይም ሠራተኛ መሆን፣

ለ) በሚሠራበት የጥብቅና ድርጅት ውስጥ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት አስፈላጊ መሆኑ በድርጅቱ ቀደም ብሎ ካልተፈቀደ በስተቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላ የጥብቅና ድርጅትን መርዳት ወይም መተባበር፣

ሐ) የግል የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፣

መ) የጥብቅና ድርጅቱ ሳያውቅና ሳይፈቅድ በራሱ ሥም የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ ከደንበኛ መቀበልና ለግል ጥቅም ማዋል፣

ሠ) ማንኛውንም ከጥብቅና ድርጅቱ ዓላማና ተግባር ጋር የሚጣረስና የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሥራ በግሉም ሆነ ተቀጥሮ መስራት፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ጠበቃ በጥብቅና ድርጅት ሸሪክ ወይም ተቀጣሪ ከመሆኑ በፊት የያዘውን ጉዳይ ደንበኛው በተለየ ሁኔታ ካልተስማማ በስተቀር በተያዘበት አግባብ ፍጻሜ ያገኛል።

29. <u>የጥብቅና ድርጅት አስተዳደር</u>

1. የጥብቅና ድርጅት በሸሪኮች ውሳኔ በተሾሙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ባላቸው ሥራ-አስኪያጆች ይተዳደራል፤
2. የጥብቅና ድርጅት ሥራ-አስኪያጅ ከድርጅቱ ሸሪኮች መካከል የሚመረጥ መሆን አለበት፤
3. የጥብቅና ድርጅት ሥራ-አስኪያጅ ድርጅቱን በዋናነት ያስተዳድራል፤ ማንኛውንም ሕጋዊ የድርጅቱን መብት ለማስጠበቅና የድርጅቱን ግዴታ ለመወጣት የጥብቅና ድርጅቱን ይወክላል፤ የድርጅቱ ተጠሪ ይሆናል፤ ድርጅቱን ወክሎ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤ ይከራከራል፤ ጠበቃ ወይም ሶስተኛ ወገን ይወክላል፤
4. የጥብቅና ድርጅቱ ሥራ-አስኪያጅ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በሚፈጸመው ስህተት ምክንያት በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ሥራ-አስኪያጁ እና የጥብቅና ድርጅቱ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ፤
5. ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት አድራሹ ሥራ አስኪያጅ ሥራውን ለማከናወን ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን የሚያውቅ የነበረ ከሆነ የጥብቅና ድርጅቱ ተጠያቂ አይሆንም፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ከተመለከተው ውጪ ከውል ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ለሚመጣ ግዴታ ኃላፊ የሚሆነው የጥብቅና ድርጅቱ ነው።

30. <u>የሥራ-አስኪያጅ ግዴታዎች</u>

1. ሥራ-አስኪያጁ በሸርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣት አለበት፤
2. የጥብቅና ድርጅት ሥራ-አስኪያጅ ድርጅቱ፣ በውስጠ ደንቦች፣ በሸርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣቱን ማረጋገጥ አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ-አስኪያጁ፡-

ሀ) አጠቃላይ የጥብቅና ድርጅቱን የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣

ለ) ከደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መቀበል እና መፍታት፤ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፣

ሐ) የድርጅቱን የሥራ ክንውን ሪፖርት የማዘጋጀትና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማቅረብ፣

መ) ድርጅቱን አዲት የማስደረግና መክፈል የሚጠበቅበትን ታክስ በታክስ ሕጉ መሠረት በወቅቱ የማሳወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት።

31. <u>የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች</u>

1. የጥብቅና ድርጅቱ በሽርክና ስምምነት ወይም ተፈጻሚነት ባለው ሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተሰወነ በስተቀር ቢያንስ ከግማሽ በላይ ድርሻ ያላቸው አባላቱ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤
2. የጥብቅና ድርጅቱ ሸሪኮች በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች የሚጸድቁት ስብሰባ ላይ ከተገኙት ሸሪኮች ቢያንስ 60 በመቶ ድርሻ ያላቸውን ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው፤
3. የጥብቅና ድርጅቱ ሸሪኮች በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የማኅበሩን መመስረቻ ጽሑፍ ለማሻሻል ስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት የሁለት ሶስተኛ ይሁንታ ድምጽ ማግኘት ይኖርበታል፤
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የጥብቅና ድርጅቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትና የውስጥ አሠራሩን በተመለከተ ውስጠ-ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

32. <u>ግብር</u>

ማንኛውም የጥብቅና ድርጅት ወይም ሸሪክ የግብር አከፋፈል አግባብነት ባላቸው የሽርክና ማኅበርን የተመለከቱ የግብር ሕጎች የሚወሰን ይሆናል።

33. <u>ህልውና እና መፍረስ</u>

1. የጥብቅና ድርጅት ህልውና በሸሪኮቹ ሞት፣ ከድርጅቱ መልቀቅ፣ ችሎታ ማጣት ወይም ሸሪኮቹን በሚያውክ ማናቸውም ለውጥ አይፈርስም፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡-

ሀ) የሽርክና ማኅበሩን ለማፍረስ ሸሪኮች ሲስማሙ፣

ለ) የጥብቅና ድርጅቱ መክሰሩ በፍርድ ቤት ሲታወጅ፣

ሐ) የሁሉም ሸሪኮቹ የጥብቅና ፈቃድ ሲሰረዝ፣ ወይም

መ) የጸና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ሸሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ሲልና ቁጥራቸው በጎደለ በስድስት ወራት ውስጥ የጸና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ሸሪኮቹ ቁጥር ቢያንስ ወደ ሁለት ካላደገ።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ (መ) ድንጋጌ ቢኖርም የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በጥብቅና ድርጅቱ የቀረው ሸሪክ ለቢሮው ጥያቄ ሲያቀርብ እና ቢሮው ጥያቄውን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የስድስት ወራቱ የጊዜ ገደብ በሶስት ወራት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር የሸሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ያለ መሆኑን የሚያውቅ ሸሪክ የጥብቅና ድርጅቱ በዚህ ሁኔታ ከስድስት ወራት በላይ ሥራውን እንዲቀጥል ካደረገ ለድርጅቱ ዕዳ እና ግዴታዎች ከጥብቅና ድርጅቱ ጋር በአንድነት እና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፤
5. የጥብቅና ድርጅት ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰረዛል፤
6. ኃላፊነቱ የተወሰነ ማኅበርን መፍረስ የሚመለከቱ በንግድ ሕጉ ወይም በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች የጥብቅና ድርጅት መፍረስን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

34. <u>የጥብቅና ድርጅት እና ሸሪኮች ኃላፊነት</u>

በሽርክና ስምምነቱ ከተፈቀደው ውጭ በያዙት ጉዳይ ላይ ያልተገባ ተግባር ካልፈፀሙ ወይም ሥራቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው ወይም በማታለል ወይም አውቀው ባደረሱት ጉዳት ካልሆነ በስተቀር ከጥብቅና አገልግሎት መስጠት ጋር

በተያያዘ በጠበቆችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች አማካኝነት በደንበኞች እና ሌላ ሶስተኛ ወገን ላይ የሚደርስ ጉዳት በጥብቅና ድርጅቱ የደረሰ ጉዳት እንደሆነ ተቆጥሮ ድርጅቱ ኃላፊነት ይወስዳል።

35. <u>ገንዘብ ጠያቂዎች</u>

1. የጥብቅና ድርጅቱ ገንዘብ ጠያቂዎች ከድርጅቱ ማናቸውም ሀብት ላይ ገንዘብ መጠየቅ ይችላሉ፤
2. ከጥብቅና ድርጅቱ ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ከሽሪኮች የግል ንብረት ላይ ገንዘብ መጠየቅ አይችሉም።

36. <u>የጥብቅና ድርጅት ግዴታዎች</u>

በዚህ አዋጅ እና በንግድ ሕጉ ስለኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር የተቀመጡት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1. ተገቢውን የሂሳብ ሠነድ መያዝ፣
2. የደንበኞቹን ምስጢር መጠበቅ፣
3. በውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ኦዲት መደረግ፣
4. ይህንን አዋጅ፣ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሕጎችና የሙያ ሥነ-ምግባር ደንቦችን ማክበር፣እና
5. በሽርክና ስምምነቱ ላይ ማሻሻያዎች ሲያደርግ ማሻሻያው በተፈረመ በ 30 ቀናት ውስጥ ለቢሮው ግልባጩን የማቅረብ እና የማጸደቅ።

37. <u>ሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት</u>

1. ማንኛውም የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ ከማኅበሩ ስለሚወጣበት ሁኔታ እና የወጣ ሸሪክን ድርሻ በተመለከተ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበርን የተመለከቱ አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
2. በዚህ አዋጅ ከሚመራው ጥብቅና አገልግሎት ድርጅት ተፈጥሮ ጋር የማይቃረኑ እስከሆነ ድረስ የንግድ ሕጉ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች በዚህ አዋጅ በሚቋቋም የጥብቅና ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>የወል ድንጋጌዎች</u>

38. <u>ስለ ክፍያ</u>

ቢሮው በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትለው በሚወጡ ህጎች መሠረት ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ለሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስከፍላቸው ክፍያዎች ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናሉ።

39. <u>ምዝገባ</u>

ቢሮው፡-

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የሰጣቸውን ጠበቆችን እና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅቶች ሙሉ መረጃ የሚይዝ እና መዝገብ ማደራጀትና እነዚህን መረጃዎች ዘመናዊ በሆነ መንገድ መመዝገብ አለበት፤
2. በምዝገባ ሥርዓቱ ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር ነጥቦች በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አዲስ የመዘገባቸውን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሥም ዝርዝር በየሶስት ወሩ ለማኅበሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፤
4. የጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸውን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች መረጃ ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን በተለያየ መንገድ ይፋ ያደርጋል።

40. <u>ከጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ጋር ስለሚሰሩ ሰዎች</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሕግ ጉዳይ ጸሐፊ፤ የጠበቃ ረዳት ወይም ሌሎች ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞችን መቅጠር የሚችል ሲሆን የጥብቅና ድርጅት ከነዚህ ከተጠቀሱት ሠራተኞች በተጨማሪ ጠበቃ ሊቀጥር ይችላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ቅጥር የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ቅጥሩ በተፈጸመ 30 የስራ ቀናት ውስጥ ለቢሮው ማሳወቅ እና ማስመዝገብ አለበት፤

3. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉትን በሕግ ጉዳይ ጸሐፊነት ወይም በጠበቃ ረዳትነት መቅጠር አይችልም፡-

ሀ) የጥብቅና ፈቃዱ የታገደን ወይም የተሰረዘን ሰው፣

ለ) ስሙ ከመዝገብ የተፋቀን ሰው፣

ሐ) ከመሥሪያ ቤቱ በዲስፕሊን ጥፋት የተባረረን ሰው፣

መ) ከሥነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ወንጀል ተከሶ የተቀጣ እና ያልተሰየመን ሰው፣

ሠ) ቋሚ ሥራ ያለውን ሰው፣ ወይም

ረ) የሕግ ትምህርት ወይም በሕግ ሙያ የሥራ ልምድ የሌለውን ሰው።

41. <u>ስለፈቃድ ዕድሳት</u>

1. የጥብቅና ፈቃድ በየዓመቱ ፈቃዱ ጸንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት፤

2. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ሳያሳድስ ከቀረ በሚቀጥለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚጣልበትን የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ ፈቃዱ ይታደስለታል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ፈቃዱን ያላሳደሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃ ካቀረበ ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ በቀጣዩ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፈቃዱ ሊታደስለት ይችላል፤

4. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ የዲስፕሊን ክስ ይቀርብበታል።

42. <u>የጥብቅና ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርቡ ማስረጃዎች</u>

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፈቃዱን ለማሳደስ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1. የግብር ክሊራንስ ማስረጃ፣

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት አስገዳጅ የሕግ ሥልጠና ከተራዘመለት ጠበቃ በስተቀር ጠበቃው በዚህ አዋጅ የተቀመጠውን የሥልጠና ግዴታ ማጠናቀቁን የሚገልጽ ማስረጃ፣

3. ለጠበቆች ማኅበር መክፈል የሚጠበቅበትን የአባልነት መዋጮ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ከማኅበሩ የሚሰጥ ማስረጃ፣

4. ዕድሜው ከ 70 ዓመት በላይ የሆነ ጠበቃ ሕጋዊ ከሆነ የጤና ተቋም የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ ያለ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ፣

5. በዓመት ውስጥ መስጠት የሚጠበቅበትን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ስለመስጠቱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣ እና

6. የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ።

43. <u>ፈቃድን ስለመመለስ</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የጥብቅና ፈቃዱን ለቢሮው በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት መመለስ አለበት፡-

ሀ) ከሙያው ውጭ በሆነ ሥራ በቋሚነት የተሰማራ እንደሆነ፣

ለ) የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ፣

ሐ) የጥብቅና አገልግሎት ለማቆም ከወሰነ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጠበቃው ፈቃድ ለመመለስ ሲያመለክት ቢሮው የጥብቅና ፈቃድ ደብተሩን ወዲያውኑ መረከብ አለበት፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠበቃው የጥብቅና አገልግሎቱን ማቋረጡን የሚገልጽ ማስረጃ ጠይቆ ከሆነ ማስረጃው የሚሰጠው ጠበቃው ከሚመለከተው አካል የግብር ክሊራንስ ማስረጃ ይዞ ሲቀርብ ይሆናል፤

4. በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃዱን የመለሰ ጠበቃ ወደ ጥብቅና ሥራው መመለስ ከፈለገ ፈቃዱን መልሶ ሊወስድ ይችላል፤ ሆኖም ጠበቃው ከጥብቅና አገልግሎቱ ከሁለት ዓመት በላይ ተለይቶ የቆየው ከሕግ ሙያ ውጪ በሆነ ሥራ ላይ ተሰማርቶ ከሆነ ፈቃዱ የሚመለስለት ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ወስዶ ካለፈ ብቻ ነው።

ክፍል አምስት

የጠበቆች የሙያ ግዴታ

ንዑስ ክፍል አንድ

ጠቅላላ የጠበቆች ግዴታ

44. ከጥብቅና ፈቃድ ጋር የተያያዘ ግዴታ

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1. በደንበኛ፣ በፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም አግባብ ባለው አካል የጥብቅና ፈቃዱን እንዲያሳይ ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፤

2. የጥብቅና ፈቃዱን በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ ሰው መጠቀሚያ ወይም መገልገያ አሳልፎ መስጠት የለበትም።

45. ስለጥብቅና አገልግሎት ውል እና ተያያዥ ግዴታዎች

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሚሰጠው የሕግ ምክር አገልግሎት ውጭ ከደንበኛው ጋር የሚያደርገውን የጥብቅና አገልግሎት ውል በጽሑፍ ማድረግ አለበት፤

2. የጥብቅና አገልግሎት ውል ማካተት ስለሚገባቸው ጉዳዮች እንዲሁም የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠን፣ ክፍያውን ለመወሰን የሚረዱ መመዘኛዎችንና የአከፋፈል ስርዓትን ጉባኤው በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚፈፀም የጥብቅና አገልግሎት ውል በአቅራቢያው ባለ ፍትህ መምሪያ ወይም ፍትህ ጽሕፈት ቤት መረጋገጥና መመዝገብ አለበት፤

4. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

ሀ) ለጥብቅና አገልግሎት መስጫ የሚሆን ቢሮ የማሟላት፣

ለ) የጥብቅና ሥራን በአገናኝ አማካኝነት ያለመስራት፣

ሐ) የጥብቅና ውልን ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ያለማቋረጥ፣ እና

መ) በጥብቅና ውሉ ከተገለጸው የክፍያ መጠን በላይ ተጨማሪ ክፍያ ከደንበኛ ያለመጠየቅ፤ ግዴታ አለበት።

46. ስለታማኝነትና ለፍትሕ አጋር መሆን

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ሥራውን በታማኝነት የመስራትና ለፍትሕ አጋር የመሆን ግዴታ አለበት፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

ሀ) ያለበቂ ምክንያት ጉዳይን ያለማጓተት፣

ለ) ምስክሮችን በሀሰት ያለማደራጀት፣ ሀሰተኛ ማስረጃ ያለማቅረብ ወይም ያለማስቀረብ፣

ሐ) ተዘጋጅቶ የመቅረብና ተገቢውን ክርክር የማድረግ፣

መ) የሕግ መሠረት የሌለውንና የማያዋጣ ጉዳይን ያለመያዝ፣

ሠ) የደንበኛውን ወይም ባለጉዳዩን ምስጢር ያለማውጣት፣

ረ) ደንበኛው ጉዳይ ደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው የማሳወቅ፣

ሰ) የጥቅም ግጭት ያለበትን ጉዳይ ከመያዝ የመቆጠብ፣

ሸ) እና ሌሎች መሰል የሥነምግባር ግዴታ አለበት፤

3. ሌሎች መሰል ከጠበቃ ሥነ-ምግባር ጋር የተያያዙ ግዴታዎች በቢሮው፣ በጉባኤው ወይም በማኅበሩ ሀሳብ አመንጪነት በቢሮው በኩል ተዘጋጅቶ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

ንዑስ ክፍል ሁለት
የሕግ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ

47. ዓላማ

የሕግ ሥልጠና ዓላማ ጠበቆች የሙያ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ወቅታዊ ዕውቀትና ክህሎት በቀጣይነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው።

48. ስለ የሕግ ሥልጠና

1. ማንኛውም ጠበቃ በዓመት ውስጥ በድምሩ ከ 24 እስከ 30 ሰዓት የሚደርስ የሕግ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ አለበት፤

2. የሕግ ሥልጠናው በተከታታይ ወይም በዚያው ዓመት ውስጥ በተለያየ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፤

3. በሕግ ሥልጠና የሚሸፈኑ የሥልጠና ዘርፎችን፣ የሥልጠና ጊዜውን ርዝመት፤ አጠቃላይ የሥልጠና አሰጣጥ መርሃ-ግብር፤ የሥልጠና ክፍያ እና ሌሎች ከሥልጠና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ማኅበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

49. እውቅና ስለተሰጣቸው ተቋማት

1. የሕግ ሥልጠና የሚሰጠው በማኅበሩ እውቅና በሚሰጠው ተቋም ይሆናል፤

2. የጥብቅና ድርጅቶች በስራቸው ያሉ ጠበቆችን ሥልጠና እንዲሰጡ በማኅበሩ እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፤

3. ማኅበሩ ለጥብቅና ድርጅት ወይም ለተቋም እውቅና ከመስጠቱ በፊት የሚሰጡ የሥልጠና ዓይነቶችን ቀድሞ ማጽደቅ ይኖርበታል፤ ሆኖም በቅድሚያ የጸደቁት የሥልጠና ዓይነቶች በማኅበሩ ወደፊት ሊሻሻሉ፣ ሊታገዱ፣ ወይም ሊሠረዙ ይችላሉ፤

4. የተከታታይ የሕግ ሥልጠና ሰጪዎች እውቅና የሚያገኙበት ሥነ-ሥርዓት እና መሥፈርቶች በተመለከተ ማኅበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

50. <u>ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት</u>

1. የሥልጠና ተቋሙ በሥልጠና ላይ ያሉትን ሠልጣኞች ሥልጠና ከጀመሩበት እንዲሁም ሥልጠና ያጠናቀቁ ሠልጣኞችን ሥልጠናውን ካጠናቀቁበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለማኅበሩ ማሳወቅ አለበት፤
2. ማንኛውም ጠበቃ ማኅበሩ ባሳወቀው የሥልጠና ጊዜ ለመሰልጠን የማያስችል በቂ ምክንያት ካለው ምክንያቱን ለማኅበሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

51. <u>የሕግ ሥልጠና አለመከታተል</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ በዚህ ንዑስ ክፍል የተቀመጡትን የሕግ ሥልጠና ግዴታዎች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ማኅበሩ ይህንኑ ለቢሮው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፤
2. ቢሮው ከተከታታይ የሥልጠና ግዴታ ጋር ተያይዞ ያለበቂ ምክንያት የሥልጠና ግዴታውን ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነ ጠበቃ ላይ የዲሲፕሊን ክስ ሊመሰርትበት ይችላል።

52. <u>የሕግ ሥልጠና ግዴታን ስለማራዘም</u>

1. ማንኛውም ጠበቃ በአሳማኝ ምክንያት ማኅበሩ በሚያወጣው የሥልጠና ጊዜ ውስጥ የሥልጠና ግዴታውን መውሰድ ካልቻለ ጠበቃው ሥልጠናውን ማኅበሩ ባወጣው ጊዜ ውስጥ መውሰድ ስላለመቻሉና የሥልጠና ጊዜው እንዲራዘምለት ማኅበሩ ከያዘው የሥልጠና ጊዜ ከአንድ ወር በፊት ቀድሞ ለማኅበሩ በማመልከቻ ማሳወቅ አለበት፤
2. ጠበቃው የሥልጠና ጊዜው እንዲራዘምለት የሚያቀርበው ማመልከቻ ሥልጠናውን መውሰድ እንዳይችል ያደረገውን ምክንያት፣ ሥልጠናውን ለመውሰድ ያደረገውን ጥረት እና በቀጣይ መቼና በምን አግባብ እንደሚወስድ ያለውን ዕቅድ የሚገልጽ መሆን አለበት፤
3. ማኅበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበለት ማመልከቻ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው የሥልጠና ጊዜውን በዚያው ዓመት ውስጥ ጠበቃው በጠየቀው ጊዜ ወይም እራሱ በመሰለው ጊዜ ሊቀይርለት ይችላል፤ ማኅበሩ ጥያቄውን ከተቀበለው የቅያሪውን ሁኔታ ወይም ጥያቄውን ካልተቀበለው ያልተቀበለው መሆኑን በ 15 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለጠበቃው ማሳወቅ አለበት፤
4. ጠበቃው በዓመት መውሰድ የሚጠበቅበትን የሕግ ሥልጠና ግዴታ በዚያው ዓመት አጠቃሎ መውሰድ ካልቻለ እና ሥልጠናውን ያልወሰደው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበና ማኅበሩ ካመነበት ጠበቃው ያልወሰደውን የሥልጠና ጊዜ ወደ ቀጣይ ዓመት በማሸጋገር በቀጣይ ዓመት መውሰድ ከሚጠበቅበት የሥልጠና ግዴታ ጋር ደርቦ እንዲወስድ ሊፈቅድለት ይችላል።

<u>ንዑስ ክፍል ሶስት</u>
<u>ስለ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ</u>

53. <u>ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ</u>

1. ማንኛውም በጥብቅና ድርጅት ውስጥ ሸሪክ ሆኖ ወይም ተቀጥሮ የሚሰራ ጠበቃ፤ ወይም በግሉ የሚሰራ ጠበቃ በዓመት እንደጉዳዩ ክብደት እና ቅለት እየታየ በዓመት ከሶስት ጉዳይ ያልበለጠ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።
2. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የሚሰጠው፡-

   ሀ) የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሰዎች፣

   ለ) ለ 3 ኛ ወገን ጥቅም ለሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ለማህበረሰብ ተቋማት፣

   ሐ) ፍርድ ቤት የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚጠይቅላቸው ሰዎች፣

መ) ሕግን፣ የሕግ ሙያን እና የፍትሕ ሥርዓቱን ለማሻሻል ለሚሰሩ ኮሚቴዎች እና ድርጅቶች ነው፤

3. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለሕዝብ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታውን መወጣቱን የሚገልጽ ማህደር መያዝ የሚኖርበት ሲሆን፤ ማህደሩም እያንዳንዱ አገልግሎት የተሰጠበትን ቀን፣ ዓይነቱን እና የተገኘውን ውጤት እና የወሰደውን ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት።

54. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ስለመምራት፣ ክትትልና ቁጥጥር

1. ቢሮው እያንዳንዱ ጠበቃ በዓመት መስጠት ከሚጠበቅበት የነጻ የጥብቅና አገልግሎት መጠን ሳያልፍ በነጻ የጥብቅና አገልግሎት ሊሰተናገዱ የሚገባቸውን ጉዳዮች እያጣራ ለጠበቆች ይመራል፤
2. እያንዳንዱ ጠበቃ በዓመት መስጠት ከሚጠበቅበት የነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ ሳያልፍ በቢሮው የሚመራለትን የነጻ የጥብቅና አገልግሎት ተቀብሎ የመስራት ግዴታ አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጠበቃው በኩል ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት መሰጠት ያለበት ሰው አግኝቶ አገልግሎቱን በነጻ የሰጠ በሆነ ጊዜ ቢሮው የአገልግሎቱን ትክክለኛነትና እውነተኛነት አረጋግጦ እውቅና ሊሰጠው ይችላል፤
4. ቢሮው የሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበሩ ቢሮው የነጻ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ የመራለትን ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አዋጅ እና በጠበቆች ሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት መፈጸሙን መቆጣጠር እና መከታተል አለበት፤
5. ማህበሩ ክትትልና ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ አገልግሎቱን በአግባቡ እየሰጠ አለመሆኑን ሲደርስበት ለቢሮው ሪፖርት ማድረግ አለበት፤
6. ቢሮው ከማህበሩ ጋር በመተባበር የተመራለትን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት በብቃትና በትጋት በመከታተል የላቀ ውጤት ለሚያስመዘግብ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በየዓመቱ ዕውቅና ሊሰጥ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
7. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ዝርዝር ጉዳዮች ይህንን አዋጅ ተከትሎ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

ንዑስ ክፍል አራት
የደንበኞች ንብረት

55. የደንበኛን ንብረት ስለማስተዳደር

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1. ከሙያ ሥራው ጋር በተገናኘ በይዞታው ወይም በአስተዳደሩ ሥር የሚገኝን የደንበኛው ወይም የሶስተኛ ወገንን ንብረት አስተዳደርን ጥበቃ ከራሱ ንብረት ፍጹም በማይገናኝበት ሁኔታ ለይቶ ማስተዳደር አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን የደንበኛው ወይም የሶስተኛ ወገን ንብረቶች የሚመለከቱ ማናቸውንም ሠነዶች ጉዳዩ ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የመያዝ ግዴታ አለበት።

56. የደንበኛ የአደራ ሂሳብ

1. በጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ እጅ የሚገኝ የደንበኛ ገንዘብ ከጠበቃው ወይም ከጥብቅና ድርጅቱ በተለየ ሂሳብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፤
2. ጉባኤው ጠበቆች ወይም የጥብቅና ድርጅቶች የደንበኞች አደራ ሂሳብ ለመያዝ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፤
3. የደንበኛው የአደራ ሂሳብ በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ማንቀሳቀስ የሚቻለው ክፍያ ሊፈፀምባቸው የሚገቡ ሥራዎች መከናወናቸውን እና በደንበኛው ሥም መደረግ ያለባቸው ወጪዎች በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፤
4. ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ የደንበኛ ወይም የሶስተኛ ወገን ጥቅም ያለበት ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ሲቀበል ለደንበኛው ወይም ለሶስተኛ ወገን ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤

5. በዚህ አዋጅ ከተመለከተው ወይም በሕግ ወይም ከደንበኛው ጋር በተደረገ ስምምነት ካልተፈቀደ በስተቀር አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለክፍያ ያልዋለ በአደራ ሂሳብ ውስጥ የተቀመጠን ገንዘብ ደንበኛው ወይም መብት ያለው ሶስተኛ ወገን ሲጠይቅ ወይም ጉዳዩ ሲጠናቀቅ ወዲያውኑ ከበቂና የተሟላ ሪፖርት ጋር ማስረከብ አለበት።

ክፍል ስድስት
የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር
ንዑስ ክፍል አንድ
ስለ ፍትህ ቢሮ

57. **የፍትህ ቢሮ ስልጣንና ተግባራት**

ቢሮው፦

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፤
2. የጥብቅና ፈቃድ፣ የጥብቅና ድርጅቶችን እና ከጠበቃ እና ጥብቅና ድርጅቶች ጋር የሚሰሩ ሰዎችን ይመዘግባል፤ የጥብቅና ፈቃድ ያድሳል፤
3. የጠበቆች ዲስፕሊን ኮሚቴ በሚወስነው መሠረት የጥብቅና ፈቃድ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤ ሌሎች ኮሚቴውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤
4. በጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች ለሚሰጡ የሕግ አገልግሎቶች ከማኅበሩ ጋር በመመካከር መለኪያዎችን ያወጣል፤
5. የሥነ-ምግባር ጥሰት ፈጽሟል ተብሎ ጥቆማ በቀረበበት ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ላይ የሥነ-ምግባር ጥሰቱ ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ ምርመራ ያደርጋል፤ የዲስፕሊን ክስ በመመስረት ለድስፕሊን ኮሚቴው ያቀርባል፤ ይከራከራል፤
6. በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለዘን ፍትህ መምሪያ በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤
7. የጠበቆች ማኅበሩ እንዲጠናከር እና ማህበሩ ከሌሎች ተቋማት ጋር ሕጋዊ ግንኙነት ስለሚፈጥርበት ሁኔታ ያመቻቻል፤
8. አዋጁን ለማስፈጸም በማኅበሩ እና በጉባኤው የሚወጡ መመሪያዎችን በማዘጋጀት እና እንዲጸድቁ በማድረግ፤ እንዲሁም አጠቃላይ የጥብቅና አገልግሎትን በተመለከተ በማኅበሩ፤ በጉባኤው ወይም ሌሎች በሚመለከታቸው አካላት የሚነሱ አዲስ ሕግ እንዲወጣ ወይም የሕግ ማሻሻያ እንዲደረግ በሚያስፈልጉ ሀሳቦች ላይ እንደ አግባብነቱ የሕግ ረቂቅ በማዘጋጀት እና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ በማድረግ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤
9. ማኅበሩ በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲደራጅና እንደተቋም ለመንቀሳቀስ እንዲችል አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤
10. ሌሎች በዚህ አዋጅ፤ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባራት ይፈጽማል።

58. **የክልሉ የጠበቆች አስተዳደር ጉባኤ**

1. የክልሉ ፍትሕ ቢሮ አካል የሆነ ጠበቆች አስተዳደር ጉባኤ ከዚህ በኋላ "ጉባኤው" እየተባለ የሚጠራው በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ጉባኤው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ ሰባት አባላት ይኖሩታል፦
   ሀ) የፍትህ ቢሮ ሃላፊ (ሰብሳቢ)
   ለ) ከክልሉ ጠበቆች ማህበር ሁለት አባላት፣
   ሐ) ከክልሉ ፍትህ ቢሮ አንድ አባል፣
   መ) ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ዳኛ፣
   ሠ) ከክልል ምክር ቤት ከህግ፣ ፍትሕ እና መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ አንድ ተወካይ፣
   ረ) ከክልሉ የፍትህ አካላት ስልጠናና ምርምር ማዕከል አንድ የህግ ባለሙያ ተወካይ፣
3. የጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ሲሆን አንድ አባል ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ መመረጥ አይችልም።

59. **የጉባኤው ሥልጣን እና ተግባራት**

ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በማኅበሩ የሚወሰዱ እርምጃዎችና ውሳኔዎች፤ እንዲሁም በማኅበሩ በሚወጡ መመሪያዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሠነዶች ሕጋዊነት ላይ ቁጥጥር የማድረግ፣
2. በማኅበሩ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ተቀብሎ መመርመር እና ውሳኔ መስጠት፣
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 64 ንዑስ ቁጥር 4 የዲስፕሊን ኮሚቴው፣ በአንቀጽ 69 መሰረት የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና በአንቀጽ 57 ንዑስ ቁጥር 1 ቢሮው በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ተቀብሎ መመርመር፣ ውሳኔ መስጠት፣
4. ቅሬታውን በሚመረምርበት ወቅት ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ይረዳል ብሎ ካመነ አዲስ ማስረጃ አስቀርቦ የማየት፣
5. የጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ ወይም ከፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቢሮው ወይም የፈተና ኮሚቴው በአግባቡ ያላጣራው ወይም ያላጤነው ፍሬ-ነገር ወይም ማስረጃ ካለ ጉዳዩን ውሳኔ ለሰጠው አካል በድጋሚ እንዲታይ ለአንድ ጊዜ መልሶ የመምራት፣
6. የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠን፣ የክፍያውን መጠን ለመወሰን የሚረዱ መመዘኛዎች እና የአከፋፈል ሥርዓትን በመመሪያ የመወሰን፣
7. ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩን የሚመረምር አጣሪ ኮሚቴ መሰየም፤ ኮሚቴው በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረትም ውሳኔ መስጠት፣
8. የአጣሪ ኮሚቴውን አሰራር የሚወስን መመሪያ ያወጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል።

60. <u>ስለ ጉባኤው ጽሕፈት ቤት እና በጀት</u>

1. ጉባኤው በፍትህ ቢሮ ውስጥ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፤
2. የጉባኤው ጽሕፈት ቤት ሰራተኞች በቢሮው ይመደባሉ፤ ጽሕፈት ቤቱ የሚሰራው ስራ ዝርዝር በጉባኤው በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
3. የጉባኤው አባላት የጉባኤውን ስራ በሚፈጽሙበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ በቢሮው ይሸፈናል፤

4. ስለ ጉባኤው በጀት አስተዳደርና ስለ ጉባኤው አባላት ክፍያ ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል።

61. <u>የጉባኤው አሠራር እና ውሳኔ</u>

1. ጉባኤው በዓመት ቢያንስ አራት ጊዜ ይሰበሰባል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰብሳቢው በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤
3. ጉባኤው የአባላቱን መደበኛ ሥራ በማይጎዳና የጉባኤውን ሥራ በማይስተጓጎል መልኩ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
4. ከጉባኤው አባላት ቢያንስ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
5. የጉባኤው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የጉባኤው ሰብሳቢ የደገፈው ወገን አብላጫ ይሆናል፤
6. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉባኤው የራሱን የውስጥ አሠራር ሥርዓት በተመለከተ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሳይቃረን በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

62. <u>በጉባኤው ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት በማህበሩ፣ በጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና ከጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በቢሮው ውሳኔ ላይ በሚቀርብ ይግባኝ መነሻ ጉባኤው በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኙን ውሳኔ ባወቀ በ 30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ መሰረት በድስፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የህግ ስህተት አለ ብሎ ካመነ የውሳኔውን ግልባጭ በወሰደ በ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

63. <u>የክልሉ ጠበቆች ዲስፕሊን ኮሚቴ መቋቋምና አወቃቀር</u>

1. የክልሉ ጠበቆች ዲስፕሊን ኮሚቴ ከዚህ በኋላ "ዲስፕሊን ኮሚቴው" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. የዲስፕሊን ኮሚቴው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ አምስት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከፍትህ ቢሮ ሁለት ተወካዮች፣

ለ) ከጠበቆች ማኅበር ሁለት ተወካዮች፣

ሐ) ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ተወካይ፣

3. የኮሚቴው ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በቢሮው ሃላፊ ይሰየማል፤
4. የአንድ አባል የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም።

64. <u>የድስፕሊን ኮሚቴው ሥልጣን እና ተግባራት</u>

ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሥራ አፈጻጸም ከሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ጋር የተጣጠመ መሆኑን መከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
2. ይህንን አዋጅ ወይም የጠበቆች የሥነ-ምግባር ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ በጠበቃ እና ጥብቅና ድርጅት ላይ የሚቀርብ ክስን ይመረምራል፤ ክሱ ጠበቃውን ወይም የጥብቅና ድርጅቱን የሚያስቀርብ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፤
3. ክሱ እና ማስረጃው ጠበቃውን የሚያስቀርብ መሆኑን ከወሰነ ጠበቃው መልሱን 15 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ እንዲያቀርብ በመጥሪያ ላይ በመግለጽ ክሱን ለጠበቃው ይልካል፤
4. በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅት ላይ የቀረበውን ክስ እና ማስረጃ፣ በጠበቃው በኩል የተሰጠ መልስ እና ማስረጃ ከመረመረ እና ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፤
5. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን የድስፕሊን ክስ የማየት ስልጣን ለዞን የጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ውክልናውም ምክንያቱ ተገልጾ በጽሁፍ መሰጠት አለበት፤
6. የጠበቆች ሥነ-ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን፤ የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለጉባኤው ሀሳብ ያቀርባል።

65. <u>የድስፕሊን ኮሚቴው አሰራርና ውሳኔ</u>

1. እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፤
2. ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤
3. ውሳኔዎችን በድምጽ ብልጫ ያሳልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ሲሆን በሰብሳቢው በኩል ያለው ድምጽ የጉባኤው ውሳኔ ሆኖ ይጸድቃል።

66. <u>የዞን ጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ</u>

1. ኮሚቴው ከክልሉ ጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ በውክልና የተሰጠውን የጠበቃ ወይም ድርጅት የድስፕሊን ጉዳይን ለማየት ከሚከተሉት አካላት የተወጣጡ በየተቋማቱ ተመርጠው የሚሰየሙ 5 አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የፍትህ መምሪያው ሃላፊ (ሰብሳቢ)፣

ለ) ከጠበቆች ማኅበር ሁለት አባላት፣

ሐ) ከፍትህ መምሪያው የሚወከል አንድ አባል፣

መ) ከከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚወከል አንድ አባል

2. የአንድ አባል የሥራ ዘመን እና የኮሚቴው አሰራርና ውሳኔ በዚህ አዋጅ ለክልሉ የጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ በተደነገገው መሰረት ይሆናል።

67. <u>የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ መቋቋምና አወቃቀር</u>

1. የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ ከዚህ በኋላ "የፈተና ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2. ፈተና ኮሚቴው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ አምስት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከፍትህ ቢሮ ሁለት አባላት፣

ለ) ከጠበቆች ማኅበር ሁለት አባላት፣

ሐ) ከክልሉ ከክልሉ የፍትህ አካላት ስልጠናና ምርምር ማዕከል አንድ አባል፤

3. የአንድ የፈተና ኮሚቴ አባል የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ በፈተና ኮሚቴ አባልነት ሊመረጥ አይችልም፤

4. የፈተና ኮሚቴው ሰብሳቢ ከአባላቱ በቢሮው ሃላፊ የሚሰየም ይሆናል።

68. <u>የፈተና ኮሚቴው ስብሰባ</u>

1. ኮሚቴው በየሩብ ዓመቱ መጨረሻ ይሰበሰባል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰብሳቢው እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበስብ ይችላል፤

3. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፤

4. የኮሚቴው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝነት ይኖረዋል።

69. <u>የኮሚቴው ሥልጣን እና ተግባራት</u>

የፈተና ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለቢሮው ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በቢሮው የጥብቅና ፈቃድ ከሚሰጠው የሥራ ክፍል ጋር በመመካከር የጥብቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና እያዘጋጀ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ለአመልካቾች ይሰጣል፤

2. የፈተናውን ሥነ-ሥርዓትና ጊዜ ይወስናል፤

3. የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፤ ለማለፊያ የሚያበቃ ነጥብ ይወስናል፤ ውጤቱን በይፋ ያስታውቃል፤

4. ፈተናውን በስኬት ላጠናቀቀ ተፈታኝ ፈተናውን ማለፉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጣል፤

5. የፈተና ሥነ-ሥርዓት ደንብ አዘጋጅቶ ለጉባኤው አቅርቦ ሲጸድቅ በሥራ ላይ ያውላል።

70. <u>ለኮሚቴዎች አባላት ስለሚከፈል ክፍያ</u>

በዚህ አዋጅ መሰረት የተቋቋሙት የጠበቆች ዲስፕሊን ኮሚቴ እና የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ ተጠሪነት በዚህ አዋጅ መሰረት ወደ ማህበሩ እስከሚተላለፍ ድረስ አባላቱ በተሰየሙባቸው ኮሚቴዎች ስብሰባ ላይ ተገኝተው ሲሳተፉ ሊከፈላቸው የሚገባው ክፍያ በሚወጣው ደንብ መሰረት በቢሮው ይሸፈናል።

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

የክልሉ ጠበቆች ማኅበር

71. መቋቋም

1. የክልሉ ጠበቆች ማኅበር ከዚህ በኋላ "ማኅበሩ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. ማኅበሩ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት አለው፤
3. ቢሮው ይህ አዋጅ ከጸናበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የማኅበሩን የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ይጠራል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተጠራው ጠቅላላ ጉባዔ የማኅበሩን አመራር አካላት ይሰይማል፤

72. ዋና መሥሪያ ቤት

የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት በሳውላ ከተማ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል።

73. ስለ ማህበሩ አባልነት

1. ማኅበሩ ሁሉንም ፈቃድ የተሰጣቸው የክልሉን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች በአባልነት ያቀፈ ነው፤
2. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከቢሮው የጥብቅና ፈቃድ ሲሰጠው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የማኅበሩ አባል ይሆናል።

74. ስለ በጀት

1. የማኅበሩ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ከአባላቱ የሚሰበሰብ መዋጮ ይሆናል፤
2. ማህበሩ ሌሎች ገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በመተዳደሪያ ደንቡ ሊወስን ይችላል፤
3. በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበሩ ከሌሎች ሕጋዊ ምንጮች የሚያገኛቸው ገቢዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ራሱን እስኪችል ድረስ ከክልሉ መንግስት የገንዘብ እና ሌሎች ድጋፎች ሊደረጉለት ይችላሉ።

75. የማኅበሩ አቋም

1. ማኅበሩ የሚከተሉት አመራር አካላት ይኖሩታል፦
   ሀ) ጠቅላላ ጉባዔ፣
   ለ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣
   ሐ) ፕሬዚዳንት እና ምክትልፕሬዚዳንት፣
   መ) ዋና ጸሐፊ፣ እና
   ሠ) ሌሎች ሠራተኞች።
2. ማኅበሩ እንደ አስፈላጊነቱ ሥራውን ለማከናወን ኮሚቴዎች ወይም በሥሩ የሚሰሩ የሥራ ክፍሎች ሊያደራጅ ይችላል።

76. የማኅበሩ ሥልጣን እና ተግባራት

ማኅበሩ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ተከታታይ የሕግ ሥልጠናን በበላይነት ይመራል፤ የተከታታይ የሕግ ሥልጠናን የሚመለከቱ የአዋጁን ድንጋጌዎች ያስፈጽማል፤
2. የተከታታይ የሕግ ሥልጠና ሰጪዎችን እውቅና ይሰጣል፤
3. ይህንን አዋጅ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በሚጥሱ የተከታታይ የሕግ ሥልጠና ሰጪዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤
4. ከተከታታይ የሕግ ሥልጠና ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ክፍያዎችን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

5. ማናቸውም የአደራ ሂሳብ አያያዝና አመራር በትክክል እየተካሄደ መሆኑን ለመቆጣጠር በማናቸውም ጊዜ የኦዲት ምርመራ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፤
6. ከአደራ ሂሳብ አያያዝ ጋር የሚነሱ የደንበኞች ቅሬታዎችን ይቀበላል፤ ማናቸውንም ሰው በማነጋገር ምርምራ ለማድረግ ይችላል፤
7. ከአደራ ሂሳብ ጋር የተያያዘ ሥራን በአግባቡ ያለመወጣት ሁኔታ ሲከሰት ጉዳዩ በዲስፕሊን ኮሚቴ ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ለቢሮው ሊመራው ይችላል፤
8. ከአደራ ሂሳብ ከሚገኝ ወለድ ወይም ማናቸውም ገቢ አጠቃቀምን አስመልክቶ መመሪያ ያዘጋጃል፤ በጠቅላላ ጉባዔው ሲጸድቅ በተግባር ያውላል፤
9. በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች ለማኅበሩ የአደራ ሂሳብን አስመልከቶ የተሠጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤
10. ስለአደራ ሂሳብ ምንነት፣ አያያዝና፣ ሪፖርት አደራረግ እንዲሁም መደረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች ተገቢው ግንዛቤ እንዲፈጠር ተከታታይ ሥልጠናዎችን ይሰጣል ወይም እንዲሠጡ ያደርጋል፤
11. ደንበኞች ጥቅም መጠበቁን ያረጋግጣል፤ እንዲሁም የደንበኞችን ጥቅም ለማስጠበቅ ጠቀሜታ ያላቸው የጠበቃ መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል፤
12. የሕግ ትምህርት ጥራት እንዲጠበቅ፤ የሕግ የበላይነት እንዲከበር፤ ሰብዓዊ መብት እንዲከበር፤ የጥብቅና ሙያ እና አጠቃላይ የሀገሪቱንና የክልሉን የሕግ ሥርዓት እንዲያድግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤
13. የጥብቅና አገልግሎትን በተመለከተ የሕግ ጥናት በማድረግ የጥናት ውጤቱን ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
14. እያንዳንዱ የማህበሩ አባል ለደንበኛው አገልግሎት የሚሰጥበት ቢሮ መኖር አለመኖሩን ይከታተላል፤ በሚያደርገው ክትትል በተሰጠው አስተያየት መሰረት ቢሮ ያልከፈተ ወይም ለመክፈት ፈቃደኛ ያልሆነ ጠበቃ ሲያጋጥመው ለቢሮው ሪፖርት ያደርጋል።
15. የማኅበሩ አባላት ነጻ የጥብቅና አገልግሎት በአግባቡ እየሰጡ ስለመሆኑ ወይም ሙያዊ ስነ ምግባራቸውን አክብረው የጥብቅና አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ከስነምግባር ውጪ የሚንቀሳቀሱትን በመለየት ለቢሮው ሪፖርት ያደርጋል።

77. <u>የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባራት</u>

ጠቅላላ ጉባዔው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጣቸውን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች በሙሉ የሚያካትት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የማኅበሩን ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ይሾማል፤ ይሽራል፤
2. የማኅበሩን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፤
3. የአባላትን መዋጮ መጠን ይወስናል፤
4. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን እና የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት ይመረምራል፤ ያጸድቃል፤
5. ለአባላቱ ጠቅላላ ጥቅም እና ለፍትሕ ተደራሽነት ጠቀሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
6. የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፤
7. በሌሎች የማኅበሩ አካላት የሚሰጡ ውሳኔዎች ከሕገ-ደብ ጥቅም እና ከማኅበሩ ዓላማ ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን ያረጋግጣል፤
8. ለማኅበሩ ሌሎች አካላት በግልጽ ባልተሰጡ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
9. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፤

10. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣኑን በከፊል ለሌላ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

11. የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤ ያሻሽላል፤ ያጸድቃል።

78. <u>የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቋም</u>

1. ማኅበሩ የአስፈፃሚነት ሥልጣን ያለው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፤

2. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰባት አባላት ይኖሩታል፤

3. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል ተመርጠው ይሾማሉ።

79. <u>የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ማኅበሩን ያስተዳድራል፤

2. የማኅበሩን ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል፤

3. የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎችን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤

4. በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

5. የሠራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤

6. የሠራተኞችን ደመወዝና አበል ይወስናል፤

7. ፕሬዚዳንቱ እና ምክትል ፕሬዚዳንቱ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

80. <u>የፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባራት</u>

1. ፕሬዚዳንቱ አጠቃላይ የማኅበሩን ሥራ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው እና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዚዳንቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፦

ሀ) ማኅበሩን ወክሎ ውል ይዋዋላል፤ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤ ማኅበሩ በሚከሰስበት፣ በሚከሰስበት ወይም በሌላ ተመሳሳይ የሕግ ጉዳይ ማኅበሩን ወክሎ የሚቀርብ ጠበቃ ይወክላል፤ የማኅበሩን ጉዳይ ማስፈጸም እንዲችል የማኅበሩን ሠራተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን እንደ አስፈላጊነቱ ይወክላል፤

ለ) የማኅበሩን ዓመታዊ እቅድ፣ በጀት፣ የሥራ ክንውን እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

ሐ) ለሥራ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ረቂቅ ያዘጋጃል፤ በሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴው ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) በማኅበሩ የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የማኅበሩን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሠ) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የማኅበሩን ሥራዎች ያሰራል፤ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት ማኅበሩን ይወክላል፤

ረ) የጠቅላላ ጉባዔና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ሰ) በጠቅላላ ጉባዔውና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡:

3.የማኅበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት፦

ሀ) ፕሬዚዳንቱ በማይኖሩበት ጊዜ ወይም ሥራውን ሊሰራ በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

ለ) በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ወይም በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

81. <u>ዋና ጸሐፊ</u>

1. ዋና ጸሐፊው በሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ የሚሾም ሆኖ ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እና ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል፤

2. ዋና ጸሐፊው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፦

ሀ) የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፤ ያከናውናል፤

ለ) የጠቅላላ ጉባዔውና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ቃለ- ጉባዔዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል ፤

ሐ) ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመማከር የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

መ) ሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በሌላ ሁኔታ እንዲፈጸም የመወሰን ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ጸሐፊው ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በመሆን የማኅበሩን የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤

ሠ) የማኅበሩን የንብረት አስተዳደር እና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት በአግባቡ መዘርጋቱን እና የሂሳብ ሠነዶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ) የማኅበሩ ንብረትና ሂሳብ ተቀባይነት ባለው የሂሳብ ዘዴ መያዙን ያረጋግጣል፤

ሸ) ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

82. <u>በማኅበሩ ውስጠ-ደንብ ስለሚወሰኑ ጉዳዮች</u>

ስለ ጠቅላላ ጉባዔው እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አመራር አካላት አደረጃጀት፣ ኃላፊነት፤ ስለ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ሌሎች ሠራተኞች የሥራ ድርሻ፣ የምርጫና ስብሰባ ሥነሥርዓት፣ የማኅበሩ ልዩ ልዩ አካላት የሥራ ዘመን እና ሌሎች ለማኅበሩ በሕግ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ማኅበሩ በሚያወጣው ውስጠ-ደንብ ይወሰናሉ።

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>የዲስፕሊን ጥፋቶች እና ቅጣት</u>

<u>ንዑስ ክፍል አንድ</u>

<u>ቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ዓይነቶች እና ቅጣቶች</u>

83. <u>ቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ዓይነቶች</u>

የሚከተሉትና መሰል በጠበቆች ሥነ-ምግባር ደንብ የተደነገጉ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈጸሙ ጥፋቶች ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡-

1. የጥብቅና ፈቃድን ለደንበኛ፤ ለፍርድ ቤት ወይም ለሚመለከተው አካል እንዲያሳይ በተጠየቀ ጊዜ ለማሳየት ፈቃደኛ ያለመሆን፣
2. በፍርድ ቤት ወይም መሰል ተቋማት የሙያ ባልደረባን መዝለፍ፣ ማንቋሸሽ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ክብሩን ለመቀነስ መሞከር፣
3. ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታና የደረሰበትን ደረጃ በደንበኛው ሲጠየቅ በአግባቡ ያለማሳወቅ፣ ደንበኛን ማመናጨቅ ወይም ክብሩን መንካት፤
4. በጠበቃ ያልተወከለ ተከራካሪ ባጋጠመው ጊዜ ጠበቃው ሆን ብሎ ይህንኑ ተከራካሪ ወገን ሊያሳስቱ የሚችሉ ድርጊቶች መፈጸም፣
5. ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮ ቀን መዘግየት እና ፍርድ ቤት ያለመገኘት፣
6. ለጠበቆች ማኅበር መክፈል የሚጠበቅበትን ክፍያ ወይም መዋጮ በተደጋጋሚ እና በወቅቱ ያለመክፈል፣

7. በሕግ ከተፈቀደው ምክንያት ውጭ ተከታታይ የግዴታ የሕግ ሥልጠና በአግባቡ አለመውሰድ፤

8. የጥብቅና ፈቃድን በወቅቱ አለማሳደስ፣

9. ባልታደሰ የጥብቅና ፈቃድ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፣

10. የጥብቅና ፈቃዱን ለጥብቅና ፈቃድ ሰጪው ተቋም ሳይመልስ በሌላ ቋሚ ሥራ ተሰማርቶ መገኘት።

84. <u>የቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 10 ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደ ጥፋቱ ሁኔታ እየታየ የሚከተሉት ቅጣቶች ይጣሉበታል።

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የቃል ማስጠንቀቂያ በዲስፕሊን ኮሚቴው ይሰጠዋል፤ ለሁለት ጊዜ የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ከፈጸመ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 3 - 6 የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 7 - 10 የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ ከብር ሁለት ሺህ እስከ ብር አምስት ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ።

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

<u>ከባድ የድስፕሊን ጥፋት ዓይነቶችና ቅጣቶች</u>

85. <u>ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ዓይነቶች</u>

የሚከተሉት እና መሰል በጠበቆች ሥነ-ምግባር ደንብ የሚጠቀሱ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈጸሙ ጥፋቶች ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተዘረዘሩ ሰዎችን በጠበቃ ረዳትነት ወይም በሕግ ጉዳይ ጸሐፊነት መቅጠር እና ማሰራት፣

2. በሥሩ የቀጠራቸውን የጠበቃ ረዳትና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ለፈቃድ ሰጭው አካል ያለማሳወቅና ያለማስመዝገብ፣

3. ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት ተለዋጭ ቀጠሮ በተደጋጋሚ መጠየቅና የፍርድ ቤት ጉዳይ እንዲጓተት ማድረግ፣

4. የጥብቅና አገልግሎት መስጫ ቢሮ ሳይኖር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

5. የደንበኛን ምስጢር አለመጠበቅ፣

6. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተው አካል ሲመራለት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን፣

7. የጥብቅና ሥራን በአገናኝ አማካኝነት መስራት ወይም ለሌሎች ጠበቆች የአገናኝነት ሥራ መስራት፣

8. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ከተደነገገው በስተቀር ከደንበኛ ጋር የሚደረግ የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነትን በጽሑፍ ያለማድረግና ያለማጸደቅ፣

9. ያለበቂ ምክንያት የጥብቅና አገልግሎት ውልን ማቋረጥ፣

10. በህግ ከተቀመጠው አግባብ ውጪ የአገልግሎት ክፍያ በመዋዋል መቀበል ወይም በጥብቅና ውሉ ከተገለጸው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ ከደንበኛው ፍላጎት ውጪ ያለበቂ ምክንያት ተጨማሪ ክፍያ መቀበል፣

11. በፍርድ ቤት ወይም ሌሎች ውሳኔ በሚሰጡ አካላት ዘንድ የሚታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ አግባብ ባልሆነ መንገድ ውሳኔ ለማግኘት መጣር፤

12. የጥቅም ግጭት የሚያስነሳ ወይም የጥቅም ግጭት ያለበት ጉዳይ መሆኑን እያወቀ ጉዳዩን መያዝ፤

13. ከተሰጠው የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ በላይ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፣

14. የደንበኛውን ማስረጃ በአግባቡ ለፍርድ ቤት ባለማቅረብ ወይም ከአቅም በታች በመከራከር መዝገቡ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፣

15. የጥብቅና ፈቃድን በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን መጠቀሚያ አሳልፎ መስጠት፣

16. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታውን እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በአግባቡ ባለመወጣት የደንበኛን ጉዳይ እንዲበላሽ ወይም ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፣

17. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 55 እና 56 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 4 እና 5 የተደነገጉትን ግዴታዎች በመተላለፍ ከደንበኛ የአደራ ሂሳብ አያያዝ ጋር የተያያዙ ጥፋቶችን መፈጸም፣

18. ከተቃራኒ ባለጉዳይ ጠበቃ ጋር በመመሳጠር ወይም ማስረጃ በማጥፋት የደንበኛ ጉዳይ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፣

19. የሕግ መሠረት የሌለውንና እንደማያዋጣ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ያዋጣል በማለት መያዝና ከደንበኛ ክፍያ መቀበል፣

20. ሀሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም ወይም በማንኛውም ሁኔታ በማታለል የጥብቅና ፈቃድ ማውጣት፣

21. ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ፣ ሀሰተኛ ምስክር በማዘጋጀት በሀሰት ማስመስከር፣ ተከሳሽ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ ወይም መምከር፣ ለተቃራኒ ወገን ጠቃሚ የሆነን ማስረጃ እንዳይጠቀምበት በማሰብ ማጥፋትና ፍትሕ እንዲዛባ ማድረግ እና የመሳሰሉ የስነ ምግባር ጥሰቶችን መፈጸም ወይም ከእነዚህ የስነምግባር ጥሰቶች ጋር በተያያዘ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፣

22. ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በእምነት ማጉደል፣ ማታለል፣ ማጭበርበር፣ ሀሰተኛ ሠነድ ማዘጋጀት ወይም መገልገል፣ ሥርቆት፣ እና በመሳሰሉት ከሥነ-ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፤

23. በታገደ የጥብቅና ፈቃድ መታገዱን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት።

86. <u>የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 ከንዑስ አንቀጽ 3 - 8 ባሉ ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች በዓመት ሁለት ጊዜ እና ከዚያ በላይ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ፤ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 ከንዑስ አንቀጽ 1 – 6 ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር አምስት ሺህ አምስት መቶ እስከ ብር አስራ ሁለት ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 ከንዑስ አንቀጽ 7- 13 ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር አስራ ሁለት ሺ አምስት መቶ እስከ ብር ሃያ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 ከንዑስ አንቀጽ 14 - 19 ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ የጥብቅና ፈቃዱ ወይም የምዝገባ ምስክር ሰርተፊኬቱ ይታገዳል፤

4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 ከንዑስ አንቀጽ 20 - 23 ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፈቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፊኬቱ ይሰረዛል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ፈጽሞ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ የጥብቅና ፈቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፍኬቱ ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ሊታገድ ይችላል፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተጠቀሰውን ቅጣት በሰባት ዓመት ውስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ የጥብቅና ፈቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፍኬቱ የሚሰረዝ ይሆናል፤

7. በዲስፕሊን ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት በወንጀል የሚያስጠይቁ የዲስፕሊን ጥፋቶችን በተመለከተ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም።

ንዑስ ክፍል ሦስት

ስለዲስፕሊን ክስ አቀራረብ፣ ይርጋ፣ ይግባኝ እና የወንጀል ቅጣት

87. ስለዲስፕሊን ጥቆማና ክስ አቀራረብ

1. አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ድርጅት የዲሲፕሊን ጥፋት ስለመፈፀሙ ጥቆማ ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለቢሮው ማቅረብ ይችላል፤
2. ቢሮው ቀረበውን ጥቆማ ወይም አቤቱታ መነሻ ምርመራ በማድረግና ማስረጃ በማሰባሰብ የድስፕሊን ክስ በማዘጋጀት ለድስፕሊን ኮሚቴው ያቀርባል፤

3. የድስፕሊን ኮሚቴው የክርክር ሥነ-ሥርዓት ጉባኤው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

88. ስለ ይርጋ

1. በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲስፕሊን ጥፋቱ በተፈጸመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፤
2. በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲስፕሊን ጥፋቱ በተፈጸመ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል።

89. ስለ ይግባኝ

1. በዲስፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የዲስፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለጉባኤው ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤
2. የይግባኝ ክርክር ሂደት በመደበኛው የወንጀል ይግባኝ አቀራረብ ሥርዓት አግባብ ይመራል፤
3. በጉባኤው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የሕግ ስህተት አለ ብሎ ካመነ የጉባኤው የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

90. የወንጀል ተጠያቂነት

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያስቀጡ የዲስፕሊን ጥፋቶች የወንጀል ድንጋጌዎችን ፍሬ ነገሮች የሚያሟሉ ከሆነ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይቀጣል።

ንዑስ ክፍል አራት

ስለ መሰየም

91. የመሰየም አቤቱታ አቀራረብ

1. በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥፋተኝነት ሪከርድ እንዲሰረዝለትና ሥሙ እንዲመለስለት መጠየቅ ይችላል፤

2. የመሰየም አቤቱታ የሚቀርበው ለዲስፕሊን ኮሚቴ ሆኖ አቤቱታው ሊቀርብ የሚችለው ቅጣቱን ከጨረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም በከባድ ድስፕሊን ጥፋት ፈቃዱ የተሰረዘበት ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የመሰየም አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው ቅጣቱ ከተጣለበት ከአራት ዓመት በኋላ ነው።

92. <u>የመሰየም ሥርዓት</u>

1. አመልካች ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የመሰየም አቤቱታውን ለዲስፕሊን ኮሚቴው ያቀርባል፤

2. የዲስፕሊን ኮሚቴውም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለቢሮው ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

3. የዲስፕሊን ኮሚቴውም የቢሮውን ወይም የሚመለከተውን አካል አስተያየት ከተቀበለና አመልካቹን በአካል በማነጋገር አስፈላጊውን ምርመራ ካደረገ በኋላ ጥፋቱ ከሪከርድ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል።

93. <u>የመሰየም ውጤቶች</u>

1. አመልካቹ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥፋተኝነት ሪከርድ ይሰረዝለታል፤

2. ሪከርዱ በማናቸውም ዓይነት ውሣኔ ላይ አይጠቀስም፤ ፈቃዱ ተሰርዞበት ከሆነ ለደረጃው የሚሰጠውን ፈተና ተፈትኖ ካለፈ እና በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ፈቃዱ ይመለስለታል፤

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 85 ንዑስ አንቀጽ 20 - 23 ሥር በተደነገጉት ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች ምክንያት የጥብቅና ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም በእነዚሁ ድርጊቶች በወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ከሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ጋር በተያያዘ በሙስና ወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ታስቦ በሚፈጸም እና ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የተሰየመ ቢሆንም የጥብቅና ፈቃዱ አይመለስለትም፤ በጥብቅና አገልግሎት ሙያ ድጋሚ መሰማራት አይችልም።

94. <u>የዲስፕሊን ኮሚቴው ስለሚሰጣቸው ትዕዛዞች</u>

የዲስፕሊን ኮሚቴው አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንዲሰየም ሲወስን ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ኮሚቴው ለሚወስናቸው ጉዳዮች መጠን ያህል ነፃ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል።

95. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

መሰየምን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ለተቀጡ ጠበቆችም ተፈጻሚ ይሆናል።

96. <u>መሰየምና ቀላል ጥፋቶች</u>

በቀላል ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የመሰየም አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልገው ቅጣቱን ከጨረሰ አንድ ዓመት በኋላ ሪከርዱ ይሰረዝለታል ወይም ቀሪ ይደረግለታል።

<u>ክፍል ስምንት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

97. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

2. ቢሮው እና ማኅበሩ በዚህ አዋጅ የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ተግባራት ለማስፈጸም የሚያስችላቸውን መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ።

98. <u>መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 ላይ የተመለከቱ ለቢሮው የተሰጡ ተግባራትን ማኅበሩ ተደራጅቶ እና ኃላፊነቶቹን መረከብ እንደሚችል ቢሮው ሲያረጋጥ ኃላፊነቶቹን ሁሉንም ወይም የተወሰኑትን መመሪያ በማውጣት ወደ ማኅበሩ ሊያስተላልፍ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው ቢኖርም ቢሮው እነዚህን ኃላፊነቶችን ካስተላለፈ በኋላ ተግባራቱ በአግባቡ ስለመፈጸማቸው መከታተል እና ኦዲት የማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ወይም እንዲወሰድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤
3. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች ወይም በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ እንደአስፈላጊነቱ ታይቶ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
4. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተሰጡ የጥብቅና ፈቃዶች መታደሳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሰረት የጸኑ ይሆናሉ።
5. በቀድሞው ክልል ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆችና የግል የህግ ጉዳይ ጸሀፊዎች ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር ደንብ ቁጥር 164/2010፣ የጠበቆች ስነ ምግባር ደንብ ቁጥር 37/97 እና የ50 ሰዓት ነጻ የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 5/2005 ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና በሌላ ህግ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

99. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ሥርዓት በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

100. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ከጸደቀበት ከታህሳስ ----- ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አርባ ምንጭ

ታህሳስ---- ቀን **2016** ዓ.ም

ጥላሁን ከበደ

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር